BIBLE
316

# መጽሐፍ ቅዱስ ምንድን ነው?

**መጽሐፍ ቅዱስ ምንድን ነው?** የሚናገርህ እግዚአብሔር ነው። ስለ እግዚአብሔር ብቻ አይደለም። ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። ከመነሳሳት በላይ ነው። በምሪት የተፃፈ (የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት) ነው። አንብበው። አድምጠው። አስብበት። ከእሱ ተማር። ለህይወትህ ተግብረው። ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ፅፏል፣ *«በድነታችሁ እንድታድጉ፣ አዲስ እንደ ተወለዱ ሕፃናት ንጹሑን መንፈሳዊ ወተት ተመኙ፤»* 1ኛ ጴጥሮስ 2፥2።

**መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?** በሦስት ቋንቋዎች (በዕብራይስጥ፣ በአረማይክ፣ እና በግሪክ) የተጻፉት ከአርባ በላይ በሆኑ ሰዎች በ1,600 ዓመታት ያህል ጊዜ ውስጥ የተፃፉት 66ቱ መጽሐፎቹ አንድ መደበኛ እና ተከታታይ ጭብጥ ያላቸው ናቸው። አዲስ ኪዳን ከ5,000 በሚበልጡ ጥንታዊ ሙሉ ወይም ያልተሟሉ የእጅ ጽሑፎች ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛነት በተፈጸሙት ትንቢቶች፣ በዘመናዊ የአርኪኦሎጂ ግኝቶች፣ በጂኦግራፊያዊ ትክክለኛነትና ዘመን በማይሽረው የምሳሌዎች ጥበብ ተረጋግጧል። መጽሐፍ ቅዱስ እስካሁን ከተጻፉት መጽሐፍት ሁሉ እጅግ በጣም ጠቃሚ እና ተጽዕኖ ፈጣሪ መጽሐፍ ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ በበርካታ ቅጂዎች ታትሞ፣ በስፋት ተሰራጭቶ፣ ወደ ብዙ ቋንቋዎች ተተርጉሞ፣ የብዙዎችን ሕይወትን የለወጠ እና ለብዙ መቶ ዘመናት የጸና ሌላ መጽሐፍ የለም። መጽሐፍ ቅዱስ ልናምነው የተገባ እና እንዴት መኖር እንዳለብን የሚያሳየን የመጨረሻው ባለስልጣን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከመጻሕፍት ሁሉ በላይ ብቻውን ጸንቶ ይቀጥላል።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ባህርያት ምንድን ናቸው?

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው። *«ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤»* 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥16።

መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነው። ኢየሱስ *«ቃልህ እውነት ነው፤ በእውነትህ ቀድሳቸው።»* ዮሐ 17፥17 ሲል ጸለየ።

መጽሐፍ ቅዱስ ዝርዝሮቹን በሚገባ በማሳየት ትክክለኛ ነው። ኢየሱስ እንዲህ አለ፦ *«እውነት እላችኋለሁ፤ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ሕግ ሁሉ ይፈጸማል እንጂ ከሕግ አንዲት ፊደል ወይም አንዲት ነጥብ እንኳ አትሻርም።»* ማቴዎስ 5፥18። የዛሬዎቹ ምርጥ የቃል-ለቃል ትርጉሞች ከ99% በላይ ትክክለኛ ይሆኑ ዘንድ የመጀመሪያዎቹ የእጅ ጽሑፎች ትክክለኛነት ተጠብቆ ቆይቷል።

መጽሐፍ ቅዱስ ንጹህ ነው። *«የእግዚአብሔር ቃል የጠራ ቃል ነው፤ ሰባት ጊዜ እንደ ተጣራ፣ በምድር ላይ በከውር እንደ ተፈተነ ብር ነው።»* መዝሙር 12፥6።

መጽሐፍ ቅዱስ ዘላለማዊ ነው። *«ሣሩ ይደርቃል፤ አበባውም ይረግፋል፤ የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።»* ኢሳይያስ 40፥8። መጽሐፍ ቅዱስ ልክ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተጻፈው ሁሉ ዛሬም ጠቃሚ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ብርቱ ነው። ዕብራውያን 4፥12 *«የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚሠራ ነውና፤ በሁለት በኩል ስለት ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፤ ነፍስንና መንፈስን፣ ጅማትንና ቅልጥምን እስኪለያይ ድረስ ዘልቆ ይወጋል፤ የልብንም ሐሳብና ምኞት ይመረምራል።»*

## ከመጽሐፍ ቅዱስ ምን የግል ጥቅሞች ይገኛሉ?

መጽሐፍ ቅዱስ ያስታጥቀናል። *«ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው።»* 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥16-17።

መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአትን እንዳንሠራ ይረዳናል። መዝ119፥9፣ 11 ይህን ማድረግ የሚቻለው እንዴት እንደሆነ ይነግረናል። *«ጕልማሳ መንገዱን እንዴት ያነጻል? በቃልህ መሠረት በመኖር ነው። አንተን እንዳልበድል፣ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።»*

መጽሐፍ ቅዱስ ለዛሬያችን (ለቀጣይ እርምጃችን) እና ለወደፊታችን (የምንከተለውን መንገድ) መመሪያ ይሰጠናል። *«ሕግህ ለእግሬ መብራት፣ ለመንገዴም ብርሃን ነው።»* መዝ 119፥105።

Amharic

መጽሐፍ ቅዱስ ጥበብን ይሰጣል። *«ቃልህ ትርጓሜ ያበራል፤ አላዋቂዎችንም አስተዋዮች ያደርጋል።»* መዝ 119፥130። ዘመን የማይሽረው ጥበብ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በምሳሌ መጽሐፍ ላይ ይገኛል።

መጽሐፍ ቅዱስ በችግር ጊዜ ይረዳናል። መዝ 119፥50 *«ቃልህ ሕያው ያደርገኛልና፣ ይህች በመከራዬ መጽናኛዬ ናት።»* በማለት ያበረታታናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ተስፋን ይሰጣል። *«በጽናትና ቅዱሳት መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ እንዲኖረን፣ ቀደም ብሎ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏልና።»* ሮሜ 15፥4።

መጽሐፍ ቅዱስ ሰላምን ይሰጣል። መዝ 119፥165 *«ሕግህን የሚወድዱ ብዙ ሰላም አላቸው፤ ዕንቅፋትም የለባቸውም።»* በማለት ተስፋ ይሰጣል።

መጽሐፍ ቅዱስ ደስታን ያመጣል። ኤርምያስ 15፥16 *«ቃልህ በተገኘ ጊዜ በላሁት፤ የሰራዊት አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤ በስምህ ተጠርቻለሁና፣ ቃልህ ሐሤትና የልብ ደስታ ሆነልኝ።»* በማለት ምሳሌ ይሰጣል።

**አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ወይም መስማት ያለበት እንዴት ነው?** ከአንድ ጥቅስ በላይ መመልከት። *«ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ»* 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥16 የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ አራቱን ዓላማዎች አስተውል። መጽሐፍ ቅዱስን እያነበብክ ወይም እያዳመጥክ እያለ እነዚህን አራት ጥያቄዎች ጠይቅ። ይህ የሚስተምረኝ ምንድን ነው? ይህ የሚወቅሰኝ እንዴት ነው? ምን እርማቶችን ማድረግ አለብኝ? ይህ የበለጠ ጻድቅ እንድሆን የሚያሰለጥነኝ እንዴት ነው?

**መጽሐፍ ቅዱስ ከሌለኝስ?** ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለመግዛት የቻልከውን ሁሉ አድርግ። መግዛት የማትችል ከሆነ፣ በርካታ ነጻ የኦንላይን ንባብ ወይም ማዳመጥ ይገኛሉ። ከጓደኛህ ወይም ከጓደኞችህ ጋር መጽሐፍ ቅዱስን መግዛት እና መጋራትን አስብበት። ወይም አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ለቡድኑ እንዲያነብ እና በትኩረት ለማዳመጥ ቤተ ክርስቲያንህን ወይም አማኝ ባልደረባዎችን ጠይቅ። *«እርሱ ግን፣ "ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚታዘዙት ናቸው" አለ።»* ሉቃስ 11፥28።

**ለመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎችና መሪዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ አንዳንድ ልዩ ጥቅሶች ምንድን ናቸው?** በቃሉ (ህያው) ውስጥ የምትኖር የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ሁን። *«ኢየሱስም በርሱ ያመኑትን አይሁድ እንዲህ አላቸው፤ "በትምህርቴ ብትጸኑ እናንተ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤"»* ዮሐንስ 8፥31። ተቀባይነት ለማግኘት መጽሐፍ ቅዱስን አጥና። *«እንደማያፍርና የእውነትን ቃል በትክክል እንደሚያስረዳ የተመሰከረለት ሠራተኛ፣ ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርብ ትጋ።»* 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፥15።

**መጽሐፍ ቅዱስ ዘላለማዊ የሆነው ለምንድን ነው?** ሐዋርያው ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈበትን ዓላማ ገልጿል። ይህ ዓላማ በሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ሊተገበር ይችላል። *«ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፉ ሌሎች ኢያሌ ታምራዊ ምልክቶችን በደቀ መዛሙርቱ ፊት አድርጓል፤ ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፣ አምናችሁም በስሙ ሕይወት እንዲኖራችሁ ይህ ተጽፏል።»* ዮሐንስ 20፥30-31። በኢየሱስ የምታምነው እና የዘላለም ሕይወት የሚኖርህ እንዴት ነው? እንዴት እንደሆነ በ www.Gospel316.org ላይ እወቅ።

**«ሣሩ ይደርቃል፤ አበባውም ይረግፋል፤ የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።» ኢሳ 40፥8።**

*መጽሐፍ ቅዱስ ምንድን ነው?* © 2025 በ John D. Morris III በ Acts One Eight ታትሟል። ይህን ሙሉ መግለጫ በማያያዝ ይዘቱን ሳትለውጥ በነጻ ማተም፣ መቅዳት፣ መለጠፍ፣ ኢሜይል ማድረግ ወይም መልእክት መላክ ትችላለህ። የአገልግሎትህን ወይም የቤተ-ክርስቲያንህን ስም ወይም አርማ በገጽ አንድ ላይ ማከል እና የእውቂያ መረጃህን ከገጽ ሁለት ግርጌ አጠገብ ካለው ጠንካራ መስመር በላይ መፃፍ ትችላለህ። Bible316 የተመሰረተው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ ነው። አላማውም ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑና የእርሱ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ ለመርዳት ነው። Acts One Eightን (ከተቻለ በእንግሊዝኛ) ወደሚከተለው ኢሜይል መላክ ትችላለህ፦ Hello@Mail316.org. በእንግሊዝኛ ቋንቋ ያልተዘጋጁ ስራቶች የትርጉም አገልግሎቶች በ www.ChristianLingua.com ላይ ቀርበዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ምንድን ነው? www.Bible316.org ላይ በ48 ቋንቋዎች በነጻ ይገኛል። በእንግሊዝኛው እትም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከሎክማን ፋውንዴሽን አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ 1995 ነው። በዚህ ትርጉም ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው።